PANORAMA # XXVI

የትዝብት አድማስ

ግንቦት 21 2000 ዓም

<u>ጽኑውን መሠረት እየመነቀሩ በድቡሽት ላይ ቤት የሚሰሩ</u>

ኢትዮጵያና ዜጎቿ ለበርካታ ዘመናት መሥዋዕትና ጊዜ በፈጀ ግንባታ ሀገራቸውን በፅናት እንዳቆዩዋት ለማንም ማስረዳት የሚያስፈልገን አይመስለንም፡፡ ሀገራቸውን ከውጭ ጠላት በመጠበቅ ነጻነቷን አስከብሮ ለማቆየት የከፈሉትን ይኽ ነው የማይባል መሥዋዕት የመዘርዘሩ ተግባር የታሪክ መዝጋቢዎች ድርሻና ሚና በመሆኑ ያንን ለማድረግም አንቃጣም፡፡ ከዚህም በቀር፥ ስለኢትዮጵያ ጥንታዊነትና ስለዜጎቿም ታላቅነት ለመጠየቅ የሚችል ማንም የሞራል ልዕልና የለውም ብለን ስለምናምን፥ በአሁኑ ወቅት በአፍራሾቿበኩል በሚያደርጉት የአጥቂነት ሂደት እኛ በተከላካይነት ብቻ ተወስነን ልንቆም የሚገባን አይሆንም፡፡ ሀገርን ለማዳን ከመከላከል አልፎ ተርፎ በግድ ወደ አጥቂነት መሸጋገር የወቅቱ አንገብጋቢና ሕዝባዊ ጥያቄ ከሆነ ዉሎ አድሯል፡፡ በኢትዮጵያ ጠላቶች በነ ወያኔዎች ጭራሽ ተጠቅተናል፥ ተንበርክከናል፥ተዋርደናል ብለን በማመን እንዲያው ከነአካቴው አሞታችን ፈስሷልና እጃችንን ሰጥተን እንገዛ ካላልን በስተቀር፥ ትግሉ በተከላካይነት ብቻ ሊወሰን አይገባውም፡፡

እየሰሩ ማፍረስ፥ እየገነቡ ማፍለስ፥ እየሰበሰቡ መበተን፥ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላቶች ዓይነተኛ ተግባርና በሂደትም እየተደረገ ያለ በመሆኑ፥ ለማነኛውም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ግለፅ ስለሆነ ፥ጥቂቶቹን ዜጎችያሳዝን እንደሁ እንጅ፥ ማንንም ሊያስቆጭ የሚችል አይደለም፡፡ ነባርና በትግሉ ፀንተው የቆዩትን ታጋዮችና ድርጅቶች እያዳከሙና እያፈረሱ፥ ለወያኔ ተጎብዳጅ የሚሆኑ ስብስቦችን መፈልፈል፥ ለኢትዮጵያ መድኅን እንደማይሆን ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ የወያኔ መሪዎች ተግባርና ዓላማ ምን እንደሆነ በአሁኑ ወቅት የማያውቅ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ተብሎ ስለማይታሰብ፥ በአሁኑ ወቅት በተለያየ ምክንያት ለወያኔ ህይወት መቀጠያ የሚሆን ድርጊት የሚፈጽሙ እነማን መሆናቸው የተሰወሩ አይደሉም፡፡ ዓላማን ለግል ጥቅም፥ የተከፈለን መሥዋዕት ለጠባብ አጀንዳ፥ ሀገራዊ ጠቅምንና ሕዝባዊ አንድነትን ለዝባዝንኪ የፖለቲካ ፕሮግራም በመለወጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቆመናል የሚሉ ፥ የማንነት ቀውስ የሚያርበተብታቸው አሳዛኝ ፍጡራን ናቸው፡፡ አንድ የተሳተ ቁምነገር ያለው ግን፥በጽናት ቆሞ መታገል የመጨረሻው ድል ተጎናፃፊ መሆኑ ነው፡፡ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ዘለቄታ ጥቅም በመቆም እስከ የመጨረሻው ድል እስከ ተገኘ ድረስ እታገላለሁ በማለት ከልቡ አምኖ የሚታገል ኃይል ምንም ቢሆን ማነኛውን ምክንያት በመስጠት ለኢትዮጵያ ጠላት ለወያኔ የሚንበረከክ አይሆንም፡፡ ይህ መሠረታዊና ዐቢይ ልዩነት የሚታረቅና የሚታጠፍ አይደለም፡፡ ይህን የልዩነት መፈክር አንግቦ እንደሚነበብ የቃላት ግጭትና የኃሳብ ፍጭት ብቻ ሳይሆን፥ በኢትዮጵያ ኅልውናና ዘላቂ

ጥቅም ላይ ያተኮረ መሠረታዊ  ልዩነት ነው፡፡ይህ ልዩነት ዛሬ በትግሉ ሂደት ሊፈታ ካልቻለ፥ ከጎልፈተ ወያኔም በኋላ እንደ ዞረ ድምር በመንከባለል ለሌላ አጋንንት በረት መክፈቻ ምክንያትና ሰበብ መሆኑ አይቀርም፡፡ ወያኔን መቃወም አሁን በኢትዮጵያ ላይ በሚያከናውነው ወንጀልና ብሔራዊ ጥፋት ብቻ ሳይሆን፥ወደፊት ለመስራት ከአቀደው ስትራተጂያዊ ዓላማና ግብ አኳያም ጭምር ሊሆን ይገበዋል፡፡ይህንን መመልከት ካልተቻለና ወያኔ ለተቃዋሚው ክፍል በሚወረውረው አጀንዳ ላይ ብቻ ማተኮሩ በወያኔ ወጥመድ መግባት መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

ወያኔ ከዘረኛ ሥርዓቱ ጋር  ከሀገረ- ኢትዮጵያ ከተወገደም በኋላ፥ ወዝፎ የሚሄዳቸው ውስብስብ ችግሮች “ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመቶ ዓመታት የቤት ሥራ ሰጥተነው እንሄዳለን” ካሉት ጋር እንዲጣጣሙ ሆነው መሰናዳታቸውን መንገንዘብ ያስፈልጋል፡፡  የኋላ-ኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊ መሆኑ የማይቀር የታሪክ ሀቅ መሆኑን ወያኔዎቹ እየመረራቸውም ቢሆን አይረዱትም ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ይህም በመሆኑ፥እነርሱ ያዋጣናል ብለው የያዙት፥ ከመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ብሔራዊ ዕርቅ አድርጎ ለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር አቀራረፅ ላይ ማተኮር ሳይሆን፥ በነፍጥ ኃይል መግዛቱን እንቀጥልበታለን የሚል ነው፡፡ ይኸ ካልተሳካ ግን፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ እራሳችንን ለመከላከል የሚያስችለንን የረዥም ጊዜ ዕቅድ ማዘጋጀት ወሳኝ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ይህን ዕቅዳቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በአሁኑ ወቅት ተግተው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡  በአሁኑ ወቅት ይህን አበክሮ አለመገንዘብ፥ ነገ ከሆነ ወዲያ ወይኔ ወይኔ  እያሉ ቢጮኹ ከታሪክ ወቀሳ ነፃ አያደርግም፡፡

ዛሬ የወያኔ መሪዎች በቅደም ተከተል በጥድፊያ የሚያከናውኗቸው አጀንዳዎች አሏቸው፡፡ የሚከተሉት ሂደቶች፥ ከበርካታ እቅዶቻቸው  መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

1. በኢትዮጵያ የምዕራቡ ክፍል ከአንድ ሰፊ፤ ለምና ስትራተጂያዊ የኢኮኖሚ አውታር የሆነውን መሬት ለሱዳን ማስረከብ ነው፡፡ ይህ በወያኔ መሪዎች በኩል የተፈፀመው ብሔራዊ ወንጀልና ክኅደት ቢያንስ ሁለት ጠቀሜታ ያስገኝልናል ብለው ይገምታሉ፡፡ ይኸውም፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላው፥ የተቃዋሚው ክፍል ደግሞ በተለይ፥ ለሀገሪቱ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ከማሰብ ተቆጥቦ፥ በጥቃቅን ዕለታዊ ችግሮች ላይ በማተኮር በየጊዜው ወያኔ በሚያቀርብለት ሰሞናዊ ፍርሽራሽ አጀንዳ ላይ እንዲረባረብ  እያደረጉ፥ በወያኔ ላይ በኅብረት እንዳይነሳ አቅጣጫን ማስለወጥ ነው፡፡  ይህ ደግሞ ወያኔዎቹ ለዘረጉት ዘላቂ ዓላማ ግብ ለመምታት ጊዜ ይሰጣቸዋል ማለት ነው፡፡

ለ) የወያኔ የመጨረሻው የመከላከያ ወረዳ የሆነውን የትግራይን መሬት በሁለንተናዊ ይዞታው  አጠንክሮ፥  ማነኛውንም ጥቃት ለመመከት

የሚያስችል ምሽግና መሰናዶ አድርጎ መጠባበቅ ወደፊት ከሚመጣው ሕዝባዊ አመፅ ሊከላከልልን ይችላል ብለው ያስባሉ። ይህ ጭራሽ የሚሆን አይደለም ብለው የሚያስቡ ክፍሎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነኝህ ወገኖች አባባላቸው ውሃ ይቋጥር አይቋጥር፥ እንደ ወያኔ ይሁዳ/ ከሃዲ ከመሆን፥እንደ ቶማስ ተጠራጣሪ መሆን በአያሌው ይሻላል ማለትን እንፈልጋለን። ያልጠረጠረ ተመነጠረ ነውና!

2. ልክ እንደ ትላንቱ፥ ዛሬም ከኢትዮጵያ ሕዝብ በስተጀርባ ተንኮል በመጠንሰስ፥ በማናለብኝ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትንና የነፃነት ልዕልና በመጣስ ከከሰላ ሱዳን እስከ ሽሬ ትግራይ የሚደርስ የባቡር ሀዲዳ በመዘርጋት ለወደፊቷ የወያኔይቱ ሪፑብሊክ ትግራይ ከውጭ ዓለም ጋር የምታደርገውን ግንኙነት ለማረጋገጥ የታለመ የፖለቲካ ስሌት መሆኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሊሰወር የሚቻል አይደለም።

3. በአሁኑ ወቅት፥ የወያኔ መሪዎች በትግራይ ግዛት ከአስር ሚሊዮን ኩንታል በላይ ሊያከማች የሚችል ጎተራ በመስራት ለአያሌ ጊዜ ሊጠቅም የሚችል እህል/ስንቅ በማከማቸት ላይ ናቸው። ይህም ከወደፊቱ ዓላማቸው መምቻ ጋር የተጣመረ ሂደት መሆኑ ሊዘነጋ የሚገባው አይደለም። ሌሎችም ለቅርብና ለሩቅ አገልግሎት ሊሆኑ የሚችሉ ቆሳቆሶች በማከማቸት ላይ ናቸው። ከመላው ኢትዮጵያ ክፍል እየተጋዘ ወደ ትግራይ የሚጓዘው ልዩ ልዩ ሀብት ለምን ዓላማ እንደሆነ መዘርዘር ያለበት አይመስለንም። የጦር መሳሪያውንና የጥይት መጋዘኑንም ብዛትና ግንባታ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚጠቀስ ጉዳይ ነው። ይህንን አባባል በትግራይ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ ነው ብለው የሥነአዕምሮ ሽልታ ልጓም ሊዘረጉ የሚችሉ ወገኖች ጥረት የማንንም አንገት ሊያስደፋ የሚችል አይደለም። ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል እንዲሉ፥ የወያኔ መሪዎች አጥፊ/ እኩይ ተግባርና የትግራይ ሕዝብ ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው መታወቅ አለበት። ከዚህም በቀር፥የነመለስ ዜናዊ የጎሳ ካርድ ጨዋታ፥ ተመዝዞ ተመዝዞ አልቆ ነፍሶበታል።

4. የኢትዮጵያን መልከዐ-ምድር /ካርታ በውዞ እንደገና ለመሳል በሚያደርጉት ጥረት ወያኔዎቹ የመጨረሻውን ሂደት አገባድደው የመደምደሚያውን ምዕራፍ በመጻፍ ላይ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። ይህንን ማሳካት ከቻልን “ ከመቶ ዓመት በላይ ዕድሜ የማታስቆጥረውን ሀገር ድምጥማጧን አጥፍተን ሌላ ቅርፅና ይዘት ያላት እንደትሆን እናደርጋታለን” ብለው ያልማሉ። ከምሥራቅ ኦጋዴንን፥ ከምዕራብ ጋምቤላን መክፈልና ማስገንጠል ማለት የደለበውን የተፈጥሮ ሀብት፥ ማለትም፥ የነዳጅ ክምችቱን፥ ማዕደናቱን፥ የከርሰ-ምድር ሀብትን ለም መሬቱንም ጭምር ሀገራችን እንዳይኖራት ማድረግ ማለት ነው። የዐባይ ምንጭ የሆነውን የጣናን ሀይቅ ከግብፅና ከሱዳን ጋር ተባብሮ መቆጣጠር ከዚህ ታላቅ ስትራተጂ/ዕቅድ ተለይቶ ሊታይ የሚችል አይደለም። ጎልም ስለማይከለከል፥ የማለም

*ቅዥታቸውን ማንም ሊከለክላቸው የሚችል አይኖርም ማለት ቢቻልም፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ይህ ሊሳካ አይችልም ተብሎ ሊደመደም የሚገባው አይደለም። ስር የሰደደ ጥላቻ የማስተዋል አዕምሮንና የአርቆ አስተዋይ ኅሊናን ስለሚያስትና ስለሚመርዝ፥ ወደ ዕብደትና ቅዠት የሚወስድ መሆኑ በወያኔ መሪዎች  መረጋገጡ የዘመናችን አስገራሚ ክስተት ከሆነ ቆይቷል። ከዚህም በላይ የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው ግን፥ሀገሪቱ ዛሬ በሞትና በሽረት ደረጃ በምትገኝበት ወቅት፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች ተቀዳሚ አጀንዳ እርስ በርስ መናኮርና መከፋፈል ነው። ጥንታዊቷንና ታሪካዊ ሀገር እንዳትጠፋ ከመከላከል ይልቅ በድቡሽት ላይ ቤት ለመስራት ይማስናሉ።  አጥፊዎቿ ይጠፏታል እንጅ፥ ዘላለማዊቷ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም እንደምትኖር ኢሕአፓና የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ጥርጥር የላቸውም። የሀገራችንን ህልውናና አንድነት ለማስከበር ደግሞ ከሁሉም በላይ፣ በይፋ ከምናውቀው ጠላት በተጨማሪ፥ የሕዝብን ጎራ ለማተራመስና ክፍፍልን አስፍነው የተሰማሩትን መሰሪዎች አጋልጦ ማውገዝና ተልዕኮአቸውን ማክሸፍ ያስፈልጋል። ድርጅቶችን እየከፋፋሉና ፀረ ወያኔ ኃይሎችን በዚህም በዚያም ለማዳከም እየተሰባሰቡ መሯሯጥ የተያያዙትን ቅጥረኞችና በተራ ጥቅም በወያኔ ተገዝተው የሕዝብን ጎራ የሚያጠቁትን ሁሉ አጋልጦ ማግለልና የሕዝብን የታጋዮችን ጎራ ማፅዳት ያስፈልጋል። ይህን ተግባር እውን ለማድረግ ሀገር ወዳድ ሁሉ በጋራና በፅናት ይነሳ።*